የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 49
ADDIS ABABA 27th July, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፮/፪ሺ፬ ዓ.ም

ለሦስተኛው የሴፍቲኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …… ገጽ ፮ሺ፫፻፸፮

CONTENTS

**Proclamation No.756/2012**

International Development Association Additional Financing Agreement for Productive Safety Net APL III Project Ratification Proclamation. …………. Page 6376

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፮/፪ሺ፬

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሦስተኛው የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፪፻፴፰ ሚሊዮን ፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሁለት መቶ ሠላሳ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው ተጨማሪ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.አ.አ ሜይ ፬ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፩ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 756/2012.

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE ADDITIONAL FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

WHEREAS, Additional Financing Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount not exceeding SDR 238,600,000 (two hundred thirty eight million six hundred thousand Special Drawing Rights) for Additional Financing Productive Safety Net APL III Project, was signed in Addis Ababa on the 4th day of May, 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 28th day of June 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለሦስተኛው የሴፍቲኔት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማኀበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፶፮/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.አ.አ ሜይ ፬ ቀን ፪ሺ፲፪ በአዲስ አበባ የተፈረመው ብድር ቁጥር 5091-ET ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፴፰ ሚሊዮን ፮፻ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሁለት መቶ ሠላሳ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Additional Financing Agreement for Productive Safety Net APL III Project Ratification Proclamation No.756/2012".

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Loan No. 5091-ET signed in Addis Ababa on the 4th day of May 2012 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for utilization of the loan amount of SDR 238,600,000 (two hundred thirty eight million six hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Additional Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of July, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**